Date - July 6, 2006
No. KIL_PR002

# የዘረኝነትን ግንብ አፈራርሰን፤ የትብብር ሃውልት አቁመናል!

ታላቂቱ ኢትዮጵያ የምትመሰረተው በሁሉም ብሄርና ብሄረሰቦች ትብብር እንጂ፤ በመለስ ዜናዊ የዘረኛ አስተዳደር ሊሆን አይችልም - ከቶውኑም። በመሆኑም ቅንጅቱ አብረውት ለመስራት ከተነሱት ሃይሎች ጋር በአጋርነት በመቆም፤ ወደፊት በኢትዮጵያ ሊመጣ የሚፈለገውን ነፃነትና ዲሞክራሲ በጽኑ መሰረት ላይ ያኖራል። ለዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎናችን እንደሚሰለፍ እናምናለን።

በአሁኑ ወቅት መለስ ዜናዊና ተከታይ ጋሻ ጃግሬዎቹ እየፈራረሰ ባለው የዘረኝነት ዳስ ውስጥ ተመሽገው፤ የሚያሰሙት የመጨረሻው የጻዕረ ሞት ጩኸት ከፓርላማ ጉንጭ-አልፋ ወሬ በመሻገር አንዳች ፋይዳ አይሰጥም። በቅርቡ የተመሰረተው "ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ" የነገዪቱን ህዝባዊት ኢትዮጵያ ለመገባት በአንድነት መቆሙ፤ በዘርና በሃይማኖት ሳይለያይ የጋራ ችግራችንን በጋራ ለመፍታት መወሰኑ፤ መላውን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊና የውጭ አገራትን ያስደሰተውን ያህል፤ የወያኔ/ኢህአዴግን ጎራ ደግሞ ፍርሃትና ብርክ ለቆበታል። የዚህ ፍርሃት ምንጭም ኢትዮጵያዊያን የዘረኝነትን ግንብ አፈራርሰው ታላቅ የትብብር ሃውልት ማቆማቸው መሆኑ ነው።

ትላንት በህዝብ ምርጫ በመሸነፋቸው በህዝብ ደም እጃቸውን የታጠቡት የወያኔ/ኢህ አዴግ መሪዎችና ተከታዮቻቸው እንጂ፤ ቅንጅቱ ወይም ትብብሩ አይደለም። ዛሬ በአሸባሪነት ተርታ የተመደበውና በውጭ ሃይሎች ፊት የተነሳው ወያኔ/ኢህአዴግ እንጂ፤ ቅንጅቱ ወይም ትብብሩ አይደለም። ዛሬ የዘር ፖለቲካ በማራመድ ህዝብን የደም አበላ ለመቀባት የተዘጋጀው የመለስ ዜናዊ አስተዳደር እንጂ፤ ቅንጅቱ ወይም ትብብሩ አይደለም። ዛሬ በህዝብ የተተፋውና በፋሽታዊ አምባገነንት፤ ስልጣኑን በጠመንጃ አፈ-ሙዝ የሚያስጠብቀው ወያኔ/ኢህአዴግ መሆኑን አለም ያወቀው፤ ፀሃይ የሞቀው ጉዳይ ነው።

ወያኔ/ኢህአዴግ ወይም መሰሎቻቸው ቀደም ሲል ከሻዕቢያ ጋር በነበራቸው ግንኙነት አገሪቱን ለጉስቁልና መዳረጋቸው ሳያንስ፤ ዛሬ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት የቆመውን ቅንጅት ለአንድነት ለዲሞክራሲ ፓርቲ፤ በለመደ አፋቸው ሊወነጅሉት መከጀላቸው ውድቀታቸውንና ውርደታቸውም ቢያሳይ እንጂ፤ ቅንጣት የፖለቲካ ትርፍ አያስገኝላቸውም። ወያኔ/ኢህአዴግና መሰል ፓርቲዎች የተነከሩበት የደም ጭቅየት እጃቸው ላይ ሳይደርቅ፤ ህዝብን ይቅርታ ጠይቀው፤ የታሰሩትን የፖለቲካ እና የህሊና እስረኞች በመፍታት ፋንታ፤ በማይወጡበት የደም አዘቅት ውስጥ መዘፈቃቸው ትላንትን ለማየት የተሳናቸው መሆናቸውን ያሳያል። እነዚህ ሃይሎች፤ ጊዜው ሳይመሻባቸው የኢትዮጵያን ችግር ከትብብሩ ጎን በመቆም በመፍታት ፋንታ፤ የጦር አበጋዞችን በህዝብ ላይ ማዝመታቸው ከታሪክ ለመማር ፈቃደኞች አለመሆናቸውን ይመሰክራል።

በአሁኑ ወቅት በዝባችን ላይ የተጫነውን ድህነትና የነፃነት እጦት ከመፍታት ይልቅ፤ "እባብና ጓጉንቸር በአንድ ይኖራሉ" እንደሚባለው ወያኔ/ኢህአዴግና መሰል ግብረ አበሮቻቸው በአንድ ድምፅ ከመንጫጫት ያለፈ ቁምነገር መፍጠር አልቻሉም። ይህ የመለስ ዜናዊ ዲስኩርና ቱማታ ደግሞ፤ የቅንጅቱና የህዝቡን ወይም የቅንጅቱንና የትብብሩን ቁርኝት ፈጽሞ የማያላላው መሆኑን በማያወላውል ሁኔታ እናረጋግጥላቸዋለን።

ህዝባችን በተፈጥሮ ያገኘውን ነፃነት ይፈልጋል። ሆኖም ይህንን ግለሰባዊ መብቱን የሚጋፉት በበዙ ቁጥር፤ በአንድነትና በትብብር በመቆም ከግለሰብ መብት ጀምሮ እስከ ወል ነፃነት ድረስ ትግሉን ይቀጥላል። ለዚህም ቅንጅት ህዝባዊ ቃል ኪዳኑን ጠብቆ ይቆማል። እንጂማ እንጂ እንደ እቶን እሳት የነደደውን የነፃነት መንፈስ ማንም፤ በምንም መንገድ አያበርደውም። በመሆኑም ቅንጅቱ ከዚህ በፊት የጀመረውንና በፍፁም እምነት የቆመለትን ሰላማዊ ትግል በመቀጠል እንደ አጥቢያ ኮከብ የደመቀ ነፃነትን ለህዝብ ለማጎናፀፍ፤ ከነፃነትና ዲሞክራሲ ሃይሎች ጋር በመተባበር ምንጊዜም ትግሉን ይቀጥላል። ለዚህም ህዝብ እና አምላክ ይረዳናል።

የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር የህዝብ ግንኙነት ክፍል።

kil@kinijitinternational.org